Summer RISE
Connecting Students to Careers

# Summer RISE 2023 Student Agreement
# ሠመር ራይዝ 2020 የተማሪ ስምምነት

Department of Partnerships
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 159, Rockville, Maryland 20850

## PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT የወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ስምምነት

ሠመር ራይዝ 2023 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ወጣት ጁንየሮች እና ለሲንየሮች በሠመር 2023 የሙያ ትምህርት እውቀት የሚገበዩበት ልምምድ እድሎችን ለመስጠት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም የምመዘገበው 2023-2024 የትምህርት ዓመት MCPS 11ኛ ክፍል ጁንየር ተማሪ ወይም 12ኛ ክፍል ሲንየር ተማሪ ስለምሆን ብቁ መሆኔን እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። ከወላጆቼ/ከአሳዳጊዬ ጋር በአንድነት ተስማምተን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ።

1. **ተረድቻለሁ** እንደ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ እስከ 5 ሳምንታት፣ መሟላት ያለበትን በሳምንት 10 ሰአት፥ በቀን 8 ሰአት ያልበለጠ፣ በሳምንት 30 ሰአት ያልበለጠ፣ በአጠቃላይ 50 ሰአት በተመደበ(ች)በት የንግድ ድርጅት፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ ወይም ተቋም (“የሙያ ልምምድ አስተናጋጅ”) ወይም በተግባር (“የሙያ ልምምድ”) ላይ በተግባራዊ የሙያ ትምህርት እድል መሳተፍ እንዳለብኝ የሥራ ልምምድ ጁን 26፣ 2023 ተጀምሮ በሳምንት እስከ አምስት ቀናት እየተካሄደ እስከ ጁላይ 28፣ 2023 በአምስት ሳምንታት ሊጠናቀቅ ይችላል። ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቀውን የተማሪ አበል ለማግኘት በሙያ ክህሎት እና በፋይናንስ ትምህርት አውደ ጥናት ላይ 50 ሰአት መሳተፍ እና ማጠናቀቅ ይጠበቅብኛል።
2. **ተረድቻለሁ** ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመመዝገቤ በፊት ሦስቱን ዋና ዋና ምርጫዎቼን ለመለየት የሙያ ፍላጎት ፕሮፋይለርን እና Naviance ላይ ያለውን ተፈላጊ የስራ ክላስተር መውሰድ እንደምችል ተረድቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቡድን ከእኔ የስራ ልምድ ፍላጎትና ምርጫ ምደባ ጋር
3. **በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ የወላጅ/አሳዳጊ ፍቃድ መረጋገጥ እና የቀጥታ ወይም ቨርቹወል ሙያዊ ክህሎቶች እና የፋይናንስ እውቀት አውደ ጥናት ላይ መሣተፍ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአታት በተጨማሪ ነው። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ተገልጾልኛል።
4. **ተረድቻለሁ** በአካል የስራ ልምምድ የምወስድበት ከተገኘ ወደ ስራ ልምምድ አስተናጋጅ ቦታ የመጓጓዝ እና የመመለስ ሀላፊነቱ የእኔ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ (5–18 እድሜ) ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመያዝ Ride On፥ Ride On Flex፥ እና አንዳንድ Metrobus መስመሮችን በነፃ ለመጠቀም ይችላሉ። የስማርት ትሪፕ ካርዶች "SmarTrip cards" ማመልከቻ "my school" እና በሌሎች ቦታዎችም ይገኛል። ስለ "Youth Cruiser SmarTrip card" ተደራሽነት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ "my College/Career Information Coordinator" ማግኘት ይቻላል እና/ወይም ይህንን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/።
5. **የሙያ ልምምዶቹ ከስራ ፍላጎቴ ጋር፣ ጂኦግራፊያዊ፣ በአካል እና/ወይም ቨርቹወል ምርጫዎቼ ጋር ሲገጣጠሙ እና በፍላጎቴ መሠረት የሚገኙ ከሆነ እንደሚመድቡኝ ተረድቻለሁ።**
6. **ተረድቻለሁ**የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን በተመለከተ የሚሻሻሉ ነገሮች ካሉ በኢሜይል እንደሚላኩልኝ በሠመር ራይዝ ቢሮ ከተገለጸልኝ በኋላ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆኑትን ኢሜሎች እና የ MCPS ኢሜሎቼን በየቀኑ መመልከት እንዳለብኝ ተገንዝቤአለሁ።
7. **ተረድቻለሁ** መርሃ ግብሬን በቀጥታ ከስራ ልምምድ አስተናጋጅ ከተመደበለኝ ሰራተኛ (የእኔ "የሙያ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች)") ጋር የማስተባበር ሀላፊነት እንዳለብኝ ተገንዝቤአለሁ።
8. **ተስማምቻለሁ**በጥሩ ሁኔታ ለመከታተል፥ ጥሩ ስነምግባር፥ ትክክለኛነት፥ ሥነ ሥርዓት፥ በፍጥነት መሥራት፥ አስተዋይነት፥ ተገቢ አለባበስ፥ እና አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር እና ቨርቹወል የምሳተፍ ከሆነ፣ ቪድኦ ላይ መሆን እንደሚጠበቅብኝ በእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ሊፈቱ የማይችሉ ጉዳዮች ካጋጠሙኝ ወይም ስጋቶች ካሉኝ፣የእኔን የሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ ወይም MCPS Summer RISE Program office summer-rise@ mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ማግኘት እችላለሁ።
9. **ተረድቻለሁ** በአካል በተገኘ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ የእኔ የሠመር ራይዝ አስተማሪ ተባባሪ/ረዳት ወይም የሠመር ራይዝ ሰራተኞች የእኔን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ እንደሚኖራቸው።
10. እኔን የስራ ልምምድ እንዳደርግ የሚቀበለኝ ተቋም ማጣሪያ እና ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖሩት እንደሚችል **ተረድቻለሁ**። ከጁን 26 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም መጀመሪያ ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ የማጣሪያ መስፈርቶችን ለማሟላት ከእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ጋር መስራት የኔ ሃላፊነት ነው። አንድ ተማሪ የአስተናጋጁን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ(ች)፣ ከተገኘ ሌላ እድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል።
11. በመረዳት ተስማምቻለሁ በኮቪድ-19 ወቅት የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከል ማእከል (CDC) መሰረታዊ መመሪያዎችን ማንበቤን እና መረዳቴን አረጋግጣለሁ፥ ይህም በሚከተለው በይነመረብ ላይ እንደሚገኝ ማወቄን፡- www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/guidance-business-response.html#more-changes. የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባለበት ወቅት በአካል ለመሳተፍ ከመረጥኩኝ ይህንን የማደርገው በራሴ ፈቃደኝነት መሆኑን ተረድቻለሁ። ይህ ስምምነት በስራ ቦታ ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ የፕሮቶኮል መስፈርቶችን እንደሚመለከት እና MCPS ከኮቪድ-19 ጋር ንክኪ ላለው ተማሪ ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ተረድቻለሁ።

12. የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ቅጥር ሰራተኛ እንደማልሆን ተረድቻለሁ። የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም አይኖርም፣ እናም አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊስተጓጎል ይችላል። የሙያ ልምምድ በሚሰጠኝ ድርጅት የእለት ተእለት ሥራ (ፋይል ማድረግ፣ ሌሎች የጽሕፈት ሥራዎችን ማከናወን፣ ወይም ደንበኞችን መርዳት) በመሣሠሉት ተግባሮች በመደበኛነትም ሆነ በቀጣይነት እንደማልሰማራ ተገንዝቤያለሁ። ለእኔ የሙያ ልምምድ የሚሰጠኝ ተወካይ የቢዝነስ/የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚመለከት መግለጫ ይሰጡኛል፥ የእኔን ሚና፥ ኃላፊነቶች፥ እና ለቢዝነሱ/ለድርጅቱ ማከናወን ያለብኝን ተግባሮች ያስተምሩኛል። ሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር በሚሠራው ሥራ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚጠቀምበትን ስልት፣ ጥራት፣ ክህሎት፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች መጠቀም የምችለዉን ሙያ ለመማር እድል ይኖረኛል።

13. ተስማምቻለሁየአጋማሽ ጊዜ እና በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም የዳሰሳ ግብረመልስ ማቅረብ እንዳለብኝ

14. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ ባጀቱ ከተገኘ ለፕሮግራሙ ወጪዎች እንደ ማካካሻ ተደርጎ የሚሰጣቸውን አበል ማግኘት እንደሚችሉ በመረዳት ተስማምተዋል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሲጠናቀቅ የአበል ቼክ ለመክፈል MCPS በወላጅ/በአሳዳጊ ፍቃድ ከተሰጠኝ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም እና የመኖሪያ ቤት አድራሻዬን አካውንቱን ለሚያስተዳድረው ባንክ ያስተላልፋል። MCPS የቤት አድራሻዬን ፈንዱን ለሚያስተዳድረው ባንክ እንዲሰጥ ፈቃድ ከመስጠት ይልቅ እንደ አማራጭ፣ ቼኩን ለመውሰድ እንድችል ወደ "Department of Partnerships office" ቢሮ እንዲላክልኝ ልጠይቅ እችላለሁ። summer-rise@mcpsmd.org የእኔን ሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ ወይም Summer RISE Program office ማግኘት እችላለሁ፥ ወይም የተማሪ ክፍያን ሂደት በተመለከተ 240-740-5599 በመደወል ጥያቄዎችን ማቅረብ እችላለሁ።

15. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ከስራ ልምምድ አስተናጋጅ ጋር እንድሰራ መብት እንደማይሰጠኝ እና እንደ ተቀጣሪነት ለመቀጠር ምንም መጠበቅ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ።

16. በሰመር ራይዝ ፕሮግራም ቪዲዮ መቀረጽ፣ ፎቶግራፍ መነሳት እና/ወይም የድምፅ መቀዳት ለኖር እንደሚችልተረድቻለሁ። እነዚህን ምስሎች እና/ወይም ሪኮርዶች ስለ ሠመር ራይዝ ለማስተዋወቅ እና ምስሎቹ ያለተጨማሪ መግለጫ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፍያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዎቹ፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ።

17. የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) በሙያ ልምምድ ውስጥ ስላለኝ ተሳትፎ ለ MCPS መረጃ ማጋራት እንደሚችሉ ተረድቻለሁ። የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ የሠመር ራይዝ ተሳታፊዎችን የሚመለከት ምንም አይነት መረጃ ለሦስተኛ ወገን አያጋራም።

18. ተረድቻለሁየዚህን ስምምነት ውሎች፣በስራ ልምድ አስተናጋጅ የተሰጡ ህጎች እና መመሪያዎችን፣ወይም ማንኛውም ሌላ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ደንቦች፣የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ህጎችን ለማክበር ካልቻልኩ ከሥራ ልምምድ ፕሮግራም ልወገድ እችላለሁ እና ድጎማውን ለመቀበልም ብቁ እንደማልሆን

19. የሚያሳስበኝ ነገር ካለ ስለ ሙያ ልምምድ፣ በፍጥነት ወደ "my Summer RISE" አስተማሪ ወይም ለ "Summer RISE Program office" በዚህ በይነመረብ ላይ summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ሪፖርት ማድረግ አለብኝ።

ስለ "Summer RISE 2023 Student Agreement"ለማመልከት የተማሪ ስምምነት ቅጽ በመመዝገቢያ ፎርም ላይ ባለዉ ሳጥን ምልክት እንዲደረግ ይገለጻል፣ እናም ይህ በኤክትሮኒክስ የምታቀርበ(ቢ)ው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ከግል ፊርማህ(ሽ) ጋር እኩል መሆኑን እንደተገነዘብክ(ሽ) ይቆጠራል።